አሐዱ ባንክ
Ahadu Bank
ከብዙዎች ለብዙዎች
Inclusive Intermediation
ahadubank.com

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

ይቻላል
It's Possible!

ፀሐይ ኢንሹራንስ አ.ማ.
Tsehay Insurance S.C.
ፀሐይ ለሁሉም ታበራለች!!
The Sun Shines For All !!
ቦሌ ድልድይ ከብራስ ሆስፒታል ፊትለፊት
Bole Bridge, in front of Brass Hospital
Tel.+251 111 11 97 70/71 +251 111 11 98 27/97 93
Fax: +251 111 11 98 86
Website: www.tsehayinsurance.com
E-mail: marketingd@tsehayinsurance.com

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

# ንግድና ልማት

ሰኔ 2015 50ኛ ዓመት እትም ☎ 011-5573544 ✉ 2458 E-mail: info@addischamber.com www.addischamber.com

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት እና አዲስ ቻምበር አብሮ መስራት የሚያስችላቸውን የመግባቢያ ሰነድ ተፈራረሙ።



የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤትና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት አብሮ መስራት የሚያስችላቸውን የመግባቢያ ሰነድ ተፈራረሙ፡፡

የመግባቢያ ሰነዱ በግሉ ዘርፍ እና በመንግስት ትብብር ንግድና ኢንቨስትመንትን ይበልጥ ለማስፋፋት የሚያስችል ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ሲሆን ሁለቱ ተቋማት ያላቸውን አቅም በማስተባበር የከተማዋን የንግድና ኢንቨስትመንት እድሎች በሀገር ውስጥና በውጪ ለማስተዋወቅ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ተገልጿል፡፡

ሁለቱም ተቋማት የጋራ እቅድ በማውጣት ስምምነቶቹን ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚሰሩ በፊርማ ስነስርአቱ ወቅት ተገልጿል፡፡

## የአዲስ ቻምበር የዳይሬክተሮች ተቋም (Institute of Directors’) ይፋ ተደረገ




**በከፍያለው ዋሲሁን**

የዳይሬክተሮች ተቋም አዲስ ቻምበር በቅርቡ መስጠት ከጀመረው አገልግሎቶች ትልቁ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ይህ አገልግሎት በኢትዮጵያ በስፋት የሚስተዋለውን የኩባንያ አመራር ክፍተትን በመሙላት ተወዳዳሪ ኩባንያዎች እውን እንዲሆኑ በር ከፋች እንደሆነ የበርካቶች እምነት ነው፡፡

አዲስ ቻምበር የዳይሬክተሮች ተቋምን በቅርቡ ይፋ ያደረገ ሲሆን በዚህ የማብሰሪያ ፕሮግራም ወቅት ከፍተኛ የመንግስት የስራ ሀላፊዎች፤ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ተወካዮች፤ የግሉ ዘርፍ ተወካዮች እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ታድመዋል፡፡

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## የቤት ግብር ተመን ማሻሻያው በአተገባበሩ ላይ ክፍተቶች እንዳሉበት የንግዱ ማህበረሰብ አባላት ገለጹ

**በከፍያለው ዋሲሁን**

ከማሻሻያው በፊት የነበረው የክፍያ መጠን እዚህ ግባ የማይባል እና የከተማዋን ነባራዊ ሁኔታ የማያንጸባርቅ እንደነበር የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ በበኩሉ አስታውቋል፡፡ ይህ የተባለው አዲስ ቻምበር የቤት ግብር ማሻሻያ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ በሚል በካሄደው የውይይት መድረክ ላይ ነው፡፡

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

MIDROC INVESTMENT GROUP
Elfora Agro Industries P.L.C.
A Member of the MIDROC Investments Group Companies



ELFORA STANDS FOR NATURAL & QUALITY PRODUCTS !
Phone: +251-116-46-10-79, +251-116-45-03-61
Fax: +251-116-45-05-03
E-Mail: elforamarketing@gmail.com
mohzeki73@gmail.com
Website: midrocinvestmentgroup.com/en

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ**

**፶0ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**

**ዋና አዘጋጅ**
አሸናፊ ምትኩ

**ዲዛይነር**
zgirma0357@gmail.com

**ዐምደኞች**
ይድነቃቸው አለማየሁ
አሸናፊ ምትኩ
ሰናይት እሸቱ
እስራኤል ማንአየ

**የኤዲቶሪያል አባላት**
ዘካሪያስ አሰፋ-ሰብሳቢ
ሲሳይ ታደሰ- አባል
ካሳሁን ማሞ- አባል
አሸናፊ ምትኩ- አባል
ስዩም ጫኔ -አባል

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ 50ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**
ሰኔ 2015 እትም

TEL. 011-5518055 | 011-5519713
011-5155221
Fax. 011-5511479 P.O.BoX. 2458

# ርዕሰ አንቀጽ

## የኢትዮጲያ የዳይሬክተሮች ኢንስቲትዩት ለመልካም የኩባንያ አስተዳደር

የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የሀገራችንን የግል ክፍለ ኢኮኖሚ ዘርፍ የሚያሳድጉና ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ በአባላቱ ላይ አተኩሮ መላውን የንግድ ማህበረሰብ ይጠቅማሉ የሚላቸውን አገልግሎቶች እንዲሰጥ የተቋቋመ ምክር ቤት ነው፡፡

ምክር ቤታችን ለአባላቱ የንግድ ድጋፍ አገልግሎት ከመስጠት በተጨማሪ አንዱና ዋነኛ ዓላማው የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚ ልማት ውስጥ ጉልህ አስተዋፅኦ እንዲኖረው ምቹ ፖሊሲ በመቀየስና የውድድር አቅም ግንባታን በማጠናከር ረገድ መንግሥት የሚያደርገውን ጥረት ገንቢ ሃሣብ በማቅረብ ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን መደገፍ ነው፡፡

አዲስ ቻምበር በስሩ ያቋቋመው የዳይሬክተሮች ኢንስቲትዩት /Inistitute of Directors-Ethiopia/ በቅርቡ እውን ሆኗል፡፡ ኢንስቲትዩቱ በዋናነት የኩባንያዎችን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትና አመራሮችን በኩባንያ መልካም አስተዳደር እና በአመራር ረገድ አቅም የሚገነባ ይሆናል፡፡

የዳይሬክተሮች ተቋም በሀገሪቱ ያለውን የኩባንያ አመራር ክፍተት በመሙላት ረገድ ትልቅ ሚና ያለው ሲሆን ስልጠናዎችን የመስጠት፣ የልምድ ልውውጥ የማከናወን እና የአመራር ጥበብን የማሳደግ አላማን ሰንቆ ወደ ስራ ይገባል፡፡ ኢንስቲትዩቱ ሀገሪቱ ማሳካት ከምትፈልገው ዘላቂ ልማት ጋር የተጣጣመ ሆኖ የአመራር እና የቢዝነስ ምህዳሩን ለማስፋት የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ ይሆናል፡፡

በምክር ቤታችን ስር ያለው የዳይሬክተሮች ተቋም በሀገራችን መልካም የኩባንያ አስተዳደር እንዲሰርጽ እና ስነ ምግባራዊ የንግድ አሰራር በሁሉም ስፍራ እንዲሰፍን የንግድ ምክር ቤቱ አባላት ተሞክሮ እንዲቀሰሙ የበኩሉን ሚና የሚጫወትና በኩባንያዎች ዘንድ ግልጽነት እና ተጠያቂነት ያለበት አሰራርን በማጎልበት በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ ሆነው የሚዘልቁበት ሁኔታ እንዲኖር በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

ኩባንያዎች በባለሙያና ተጠያቂ በሆኑ የቦርድ አባላት እንዲመሩ የማድረግ ስራና ኩባንያዎች ማህበራዊ ሀላፊነታቸውን እንዲወጡ ማስተማርና ግንዛቤ ማስጨበጥ ከሚያከናውናቸው አበይት ተግባራት መካከል አንዱና ዋናው ነው፡፡

ተቋሙ የኩባንያዎችን አቅም በመገንባት ረገድ ለከፍተኛ አመራሩ ስልጠና ከመስጠት ባሻገር ለአባላት መሰረታዊ የሚባሉ በንግዱ ህብረተሰብ ተግዳሮት ዙሪያ ያሉ ጉዳዮች ማለትም በስነ ምግባርና በኩባንያ መልካም አስተዳደር ላይ ያላቸውን ትስስር፤እንዲሁም ከአካባቢ ጥበቃ አንጻር ስልጠናዎችን መስጠት እና መሰረተ ሰፊ የአድቮኬሲ ስራ የሚሰራ ይሆናል!

# የአዲስ ቻምበር የዳይሬክተሮች ተቋም (Institute of Directors’) ይፋ ተደረገ

ከ ገጽ 1 የዞረ

በዚህ የማብሰሪያ ፕሮግራም ወቅት ከንግድ ምክር ቤቱ የዳይሬክተሮች ተቋም ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ባለ ድርሻ አካላት አዲሱን አገልግሎት አስመልክቶ ንግግር አድርገዋል፡፡ ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ የምክር ቤቱ ፕረዚደንት የመክፈቻ ንግግር ካደረጉት እንግዶች መካከል አንዷ ናቸው፡፡ ዳይሬክተርነት ቁልፍ ከሆኑ የአመራር ሚናዎች መካከል አንዱ ሲሆን ይህ ሚና እውቀትን በማስፋት የሙያ ተወዳዳሪነት በማሳደግ እንዲሁም ክህሎት እንዲያድግ በማድረግ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው በማለት ተናግረዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የኩባንያ መልካም አስተዳደር እውን እንዲሆን ደንቦችና አሰራሮች ተግባራዊ እንዲደረጉ በማስቻል የዳይሬክተርነት ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ በተለይም አሁን በምንኖርበት አለም የቢዝነስ አውድ በከፍተኛ ሁኔታ በሚለዋወጥበት አለም አቅም ያላቸው የዳይሬክተሮችና አመራሮች ሚና ወደር የማይገኝለት ነው ፤ ተቋማት በዘላቂነት እንዲቀጥሉ ከተፈለገ ብቃት ያላቸው አመራሮችና ዳይሬክተሮች ሊኖሩን ይገባል በማለት ተናግረዋል፡፡ የዳሬክተሮች ኢንስቲትዩት መቋቋም ብቃት ያላቸውን የቦርድ አመራር አባላትን ለማፍራት የላቀ ጠቀሜታ ይኖረዋል በማለት የተናገሩት ደግሞ የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን ዳይሬክተር ጀነራል ብሩክ ታዬ( ዶ/ር) ናቸው፡፡

የቦርድ አመራርን የሚያሰለጥን ፣ የሚያስተምር ፣ ዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው ተቋም በኢትዮጵያ አልነበረም ያሉት ብሩክ (ዶ/ር) ይህም በመንግስት የልማት ድርጅትም ሆነ በግል የንግድ ድርጅቶች ውስጥ ብቃት ያላቸውን የቦርድ አመራሮች ማፍራት ላይ ክፍተት እንደነበር አስታውሰዋል፡፡

በተለይ በካፒታል ገበያ ላይ ኢንቨስት የሚያደርጉ ባለሃብቶች ፤ ገንዘባቸውን ከማፍሰሳቸው በፊት









በቅድሚያ ኩባንያው ምን አይነት ቦርድ አባላት አሉት ፣ ቦርዱስ ምን ያህል ጠንካራ ነው የሚለውን ይጠይቃሉ ያሉት ብሩክ ( ዶ/ር) ኢንስቲትዩቱ እነዚህን ጥያቄዎች በመመለስ ለካፒታል ገበያ የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለዋል፡፡

ይህንን ያሉበትን ምክንያት ሲያብራሩ ኢንቨስተሩ የባለአክሲዮኑ ኃላፊ በመሆን ዋና ስራ አስፈፃሚውን ብሎም አስተዳደሩን (ማኔጅመንቱን) የሚቆጣጠርበት አሰራር በመሆኑ ነው ብለዋል፡፡

የንግድ ኩባንያዎች ብቃትና ክህሎት ባላቸው የቦርድ አባላት ካልተመሩ ለድርጅቶች ፈተና ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡ አዲስ ቻምበር ተነሳሽነቱን ወስዶ የዳሬክተሮች ኢንስቲትዩት ማሰልጠኛ አቋቁሞ ወደ ስራ መግባቱ አቅምና ብቃት ያላቸው የቦርድ አመራሮች የሚወጡበት እንደሚሆን ያላቸውን ተስፋ ተናግረዋል፡፡ አክለውም የሰለጠኑና ክህሎት ያላቸው ግለሰቦች የቦርድ አባል ሆነው መቀመጣቸው በኢትዮጵያ ሊጀመር ለታሰበው የካፒታል ገበያ ከፍተኛ እድል ይሰጣል ብለዋል፡፡

የካፒታል ገቢያ ትልቁ ሚና ሃብት ማሰባሰብ ነው ያሉት ብሩክ ( ዶ/ር ) ፣ በመሆኑም ቦርድ ላይ የተቀመጡ ሰዎች ጠንካራና ድርጅቶችን በስነ-ሰርዓት የሚመሩ ከሆነ ለኢኮኖሚው ከፍተኛ አስተዋፆ ያደርጋል በማለት በመክፈቻ ንግግራቸው ወቅት ተናግረዋል፡፡

የዳይሬክተሮች ኢንስቲትዩት ይፋ በተደረገበት ወቅት ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ምክትል ፕረዚደንት አቶ ሰለሞን ደስታ ናቸው፡፡ ለዳሬክተሮች ኢንስቲትዩት አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን የባንኩ ምክትል ገዢ የገለፁ ሲሆን የኩባንያ መልካም አሰተዳደር ለገቢያ መር ኢኮኖሚ በተለይም ለፋይናንስ ብሎም ለአጠቃላይ የንግድ ከባቢ አዎንታዊ አስተዋፆ ያበርክታል በማለት አክለው ገልጸዋል፡፡

አቶ ሰለሞን አክለውም በኮርፖሬት ቢዝነስ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ጠንካራና ሚዛኑን የጠበቀ የዳሬክተሮች ቦርድ አስፈላጊ መሆኑን አስምረውበታል፡፡ በአግባቡ የሚመሩ ኩባንያዎች ከፍተኛ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ዓላማቸውን እንዲያሳኩ እንደሚያስችላቸውም ያላቸውን እምነት ገልፀዋል፡፡

ታዲያ ይህንን ለማሳካትና የአንድን ኩባንያ አስፈፃሚ አመራሮችን ለመቆጣጠር ተወዳዳሪና ብቃት ያለው የዳሬክተሮች ቦርድ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ በተለይ በግሉ ዘርፍ ያለውን የኩባንያ አመራር ከተለምዷዊ አሰራር በማውጣት የዳሬክተሮች ቦርድ አመራር የኩባንያ መልካም አስተደዳር በማዘመን ፣ በባለሙያ እንዲመራ በማድረግ የአዲስ ቻምበር አመራሮች የሰጡትን ጠንካራ የአመራር ቁርጠኝነት አድንቀዋል፡፡ ንግድ ምክር ቤቱ ያቋቋመው የዳሬክተሮች ኢንስቲትዩት ለቦርድ አባሎቻችን ፣ ቦርድ ሰብሳበቢዎችን ፣ ስራ አስፋፃሚዎችና የቢዝነስ አመራሮች ዘንድ ለውጥ ለማምጣት ልምድ የሚካፈሉበትና የሚወያዩበት በመሆኑ ከፍተኛ ቦታ እንደሚሰጡት ተናግረዋል፡፡

አዲስ ቻምበር የጀመረውን የዳይሬክተሮች ኢንስቲትዩት እውን እንዲሆን በትብብር ከሚሰራባቸው ተቋማት መካከል በኬንያ የሚገኘው የሀገሪቱ የዳይሬክተሮች ተቋም አንዱ ሲሆን የተቋሙ ዋና ሊቀመንበር የሆኑት ኔልሰን ኩርያ (ዶ/ር) ባደረጉት ንግግር የረጅም አመት ልምዳቸውን አካፍለዋል፡፡ የዳይሬክተሮች ተቋም በኢትዮጵያ እውን መሆን ከፍተኛ ደስታ እንደፈጠረላቸው የሚናገሩት ኔልሰን ኩርያ (ዶ/ር) ከአዲስ ቻምበር ጋር በጥምረት ለመስራት ያላቸውን ፍላጎት ተናግረዋል፡፡

ዳይሬክተርነት ስልጣን ብቻ ሳይሆን አንድ ተቋም አምኖበት የሚሰጠው ልዩ ስጦታ ነው ስለሆነም ይህን ማእረግ በአግባቡ በመጠቀም ብቃት ያለው አመራርን ተግባራዊ ማድረግ ብሎም ዜጎች የተሻለ ህይወት እንዲመሩ እንዲሁም ጠንካራና ተወዳዳሪ የቢዝነስ ተቋማትና ኩባንያዎች እንዲፈጠሩ ማደረግ ያስፈልጋል ኔልሰን ኩርያ ተናግረዋል፡፡

በደማቅ ሁኔታ የተበሰረው የአዲስ ቻምበር የዳይሬክተሮች ተቋም የምክር ቤቱ ዋና ጸሀፊ የሆኑት አቶ ሺበሺ ቤተማርያም የአዲሱን አገልግሎት የስትራቴጂ ግቦች ራእይና ተልእኮን አስመክተው ሰፊ ገለጻ አድርገዋል፡፡

በመጨረሻም የዳይሬክተሮች ተቋምን የተመለከተ የፓናል ውይይት የቀረበ ሲሆን በዘርፉ ሰፊ ልምድ ያላቸው እንግዶች ውይይት አካሂደዋል፡፡

# የታዳሽ ሀይል አቅርቦት ለአፍሪቃ

በአሸናፊ ምትኩ

እንደ አፈሪቃ ልማት ባንክ የቅርብ ጊዜ ሪፖርት 640 ሚሊዮን አፍሪቃውያን የኤልክትሪክ አቅርቦት የላቸውም፡፡ በሌላ አገላለጽ 40 ከመቶ የሚሆኑ አፈሪቃውያን ብቻ ናቸው የኤልክትሪክ አገልግሎት ማግኘት የቻሉት፡፡ ይህ ቁጥር ከአለም ሀገራት ጋር ሲነጻጸር እጅግ ዝቅተኛ እንደሆነ ይነገራል፡፡

ኢትዮጵያን ጨምሮ በአፍሪቃ ከሰሀራ በታች ባሉ ሀገራት የሚገኙ ሀገራት እንደ ምግብ ማብሰያ የመሳሰሉ የሀይል አማራጮችን የሚያገኙት ከከሰል ድንጋይ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ታዲያ ዜጎች የሀይል ፍላጎታቸውን ለሟሟላት ሲሉ እንደ ደን የመሳሰሉ የተፈጥሮ ሀብትን በመመንጠር የአለም ሙቀት አሁን ካለበት የበለጠ እንዲጨምር አሉታዊ ተጽእኖ በመፍጠር ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህ የተነሳ የአለም ስነ ምህዳር አደጋ ውስጥ እየገባ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ እንደ አፍሪቃ ኢነርጂ ቻምበር ሪፖርት በርካታ የአፍሪቃ ሀገራት የሀይል ፍጆታቸውን ከከሰል ድንጋይ ማድረጋቸውን አረጋግጧል፡፡

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ንግድ ም/ቤቱ ለከፍተኛ የኩባንያ መሪዎች ስልጠና መስጠት ጀመረ

በአዲስ ቻምበር እና በኬንያው የዳይሬክተሮች ተቋም በጋራ የተዘጋጀው ስልጠና የኩባንያ የቦርድ አባላት እና የማኔጅመንት መሪዎች ሚናቸውን እና ኃላፊነታቸውን በብቃት እንዲወጡ ያግዛል ተብሏል። ሥልጠናውን በይፋ ያስጀመሩት የንግድ ም/ቤቱ ዋና ጸሐፊ አቶ ሺበሺ ቤተማሪያም ለረዥም አመታት የአገራችን ኩባንያዎች በልምድ የሚተዳደሩ እና በቤተሰብ አባላት የሚመሩ ናቸው። ነገር ግን ውድድር የበዛበት የዓለም ንግድ ሥርዓት ጋር አብሮ ለመሄድ እና ብቁ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት የቢዝነስ ድርጅቶች አመራር ሥልጠና በጣም አስፈላጊ እየሆነ መጥቷል ብለዋል።

ንግድ ምክር ቤቱ ሥልጠናውን የሚሰጠው በአባላቱ እና በመላው የንግዱን ዘርፍ አባላት ዘንድ የዘመናዊ የቢዝነስ አመራር በተለይም የመልካም የኩባንያ አስተዳደር ባሕል እንዲያድግ በማሰብ ነው። በዚህ መሠረት በንግድ ም/ቤቱ ስር የተቋቋመው አዲሱ የዳይሬክተሮች ተቋም በዋናነት በሙያ ብቁ እና በሥነ ምግባር አርአያ የሆኑ የቢዝነስ መሪዎችን ለማፍለቅ ትልቅ ሚና አለው ብለዋል።

የኬንያ ዳይሬክተሮች ተቋም ኃላፊ ሜሻክ ጆራም በበኩላቸው የቢዝነስ፡ ኩባንያ መሪዎች ከተለያየ የሙያ ዘርፎች የመጡ እና የሰፋፊ ተሞክሮዎች ባለቤት ናቸው። ነገር ግን በአገር ደረጃ ወጥ የሆነ የኩባንያ አመራር ባሕል፤አሰራር እና አመራር እንዲኖር የዳይሬክተሮች ስልጠና በጣም አስፈላጊ ነው ብለዋል። በተቋሙ የሚሰጡ ስልጠናዎች በአክሲዮን ባለድርሻዎች፤ በቦርድ አባላት እና በማኔጅመንት መሪዎች ማካከል መልካም የሥራ ግንኙነት፤ ትብብር እና መተማመን እንዲኖር ይረዳሉ ብለዋል።

በስልጠናው ተሳታፊ ከነበሩት የአዋሽ ባንክ የቦርድ አባል እና የቀድሞው የአዲስ ቻምበር ፕሬዝደንት አቶ ኤልያስ ገነቲ በበኩላቸው ስልጠናው የአመራር ጥበባትን ፤ዘመናዊ ቢዝነስ አሰራሮች እንዲሁም የግጭት አፈታት ዘዴዎችን ለመቅሰም ያግዛል። የቦርድ አባላት እና የማኔጅመንት መሪዎች ዛሬ ላይ ሆነው ነገ የሚጠብቃቸውን ውድድር በማሰብ ራሳቸውን በመረጃ እና በእውቀት ማጎልበት አለባቸው ብለዋል።

ስልጠናው ለ5 ተከታታይ ቀናት የቆየ ሲሆን በቢዝነስ ስትራተጂካዊ አመራር፤ በሰው ኃይል እና በሃብት አመራር ጥበብ፤ የኮሚዩኒኬሽን ክህሎት በማሳደግ እንዲሁም የኩባንያዎች ምርጥ ተሞክሮችን ማካፈል የሚሉት አርዕስት ከስልጠናው ትኩረቶች መካከል እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል።

# አዲስ ቻምበር 24 ሰዓት የሚተላለፍ የማህበረሰብ ሬዴዮ ፕሮግራም ለመጀመር በዝግጅት ላይ መሆኑን የምክር ቤቱ ዋና ፀሀፊ አስታወቁ



የምክር ቤቱ ዋና ፀሀፊ አቶ ሺበሺ ቤተ ማርያም ይህንን ያስታወቁት የአዲስ ቻምበር የሚዲያ ቀን ሲያከብር ነው።

አቶ ሺበሺ ንግድ ምክር ቤቱ 76ተኛ አመቱን ማስቆጠሩን አውስተው ንግድና ኢንቨስትመንት በኢትዮጵያ ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ በርካታ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል ብለዋል።

የምክር ቤቱ ስራዎችን ለማስተዋወቅ ከመንግስትና የግል ሚዲያዎች ጋር አብረን መስራታችንን እንቀጥላለን ያሉት አቶ ሺበሺ ለዚህም ማሳያ አዲስ ቻምበር ከፋና ብሮድ ካስቲንግ ኮርፖሬትና ከኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ መፈራረሙን ጠቅሰዋል።

የፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ አድማሱ ዳምጠው በበኩላቸው ለሁለንተናዊ እድገት በጋራ ስንሰራ አብረን እናድጋለን ያሉ ሲሆን ከአዲስ ቻምበር ጋር የመሰረቱት ግንኙነት የንግድ ምክር ቤት ስራዎች ተደራሽ እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ ተቋማቸው እንደሚሰራ ገልፀዋል። ፋና ብሮድካስቲንግ መሪ ቃሉ ‹በሕይወት ፈጥነት› የሚል መሆኑን አስታውሰው መረጃዎችን ተደራሽ ለማድረግ እንደሚሰሩ አረጋግጠዋል። እክለውም ሁላችንም የተለያዩ ሚዲያዎች ላይ የምንሰራ ቢሆንም ሳንገፋፋና አንዳችን ለሌላኛው ጋር አብረን ልንሰራ ይገባል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

በንግድ ምክር ቤቱ የሚዲያ ቀን ላይ የህትመትና የብሮድካስት ሚዲያ አመራሮች እንዲሁም ጋዜጠኞች ተገኝተዋል።

# አዲሱ የኦንላይን ጨረታ አሰራር በነጋዴው እይታ

**በይድነቃቸው አለማየሁ**

የመንግሥት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር ባለሥልጣን በቅርቡ በጠራው የምክክር መድረክ ላይ የተሳተፉ አቅራቢ ነጋዴዎች መንግሥት ባለፈው አመት የጀመረው የኦንላይን ጨረታ ሥርዓት ሁሉን አቅራቢዎች እኩል ተሳታፊ እንዲሆኑ ዕድል የሚሰጥ ነው ተብሎለታል። በሌላ አነጋገር የመንግሥት መ/ቤቶች በየበጀት አመት መጀመሪያ ላይ የሚያወጡት የግዢ ጨረታ ሁሌም ከውስጥም ከውጪም ለትችት ተዳረገ ነው። የመንግሥት ዕቃ ግዢ ሠራተኞች እስከ በላዮች ድረስ በተዘረጋው የጥቅም ሰንሰለት አማካኝነት ጥራታቸው የወረደ ቁሳቁስ እና ደካማ አገልግሎቶች እየተገዙ ማየት የተለመደ አሰራር ነበር።

በዚህ ጠያቂም ተጠያቂም ሳይኖር የሕዝብ ሃብት ያለጠያቂ ሲባክን የጥቂቶችን ኪስ ሲያወፍር ቆይቷል። ይህ ብልሹ አሰራር የብዙ ሕጋዊ እና ሐቀኛ ነጋዴዎች የምሬት አውድ ሆኖ ኖሯል። በዙዎችም በፍትሀዊ ውድድር ማጣት ምክንያት ከስረው ከሥራ ገበያ ወጥተዋል። ዛሬ ላይ ግን ሁኔታው ተቀይሯል። መንግሥት በባለፈው ዓመት በጀመረው የኦንላይን የጨረታ ሥርዓት ለሕገወጦች በሩ የተዘጋ ይመስላል።

በቅርቡ የመንግሥት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን በአዲስ አበባ ከሚገኙ ነጋዴዎች ጋር ውይይት አካሂዷል። ተሳታፊ ነጋዴዎች እንደሚሉት ዘመናዊው የኦንላይን የጨረታ ሥርዓት በተለይ አቅራቢ ነጋዴዎችን ደስ ያሰኘ እንደሆነ ለመረዳት ችለናል።

በዚህ የውይይት መድረክ ላይ የተሳተፉ የንግድ ማህበረሰብ አባላት በአዲሱ የኦንላይን የጨረታ አሰራር ደስተኞች መሆናቸውን ለአዲስ ቻምበር ድምጽ በሰጡት ቃለመጠየቅ ተናግረዋል።

በስራ ላይ ያለው የኦንላይን ጨረታ ፖርታል ለሁሉም ተመዝጋቢ ነጋዴ 24 ሰአት እና በሳምንት 7ቱን ቀናት ክፍት መሆኑ እንዲሁም የተጫራቾችን መረጃ በምስጢር የሚይዝ በመሆኑ የበርካታ ነጋዴዎችን እሮሮ እንዳስቀረ በባለሙያዎች ተነግሯል።

ከአቅራቢዎች አንጻር የጨረታው ፖርታል አንዳንድ ነገሮች ይቀሩታል። በተለይ በፓኬጅ የሚቀርቡ አገልገሎቶችን ልብ ይሏል።

ከባለስልጣኑ በተገኘው መረጃ መሠረት የዚሁ የኦንላይን ጨረታ ግዢ ሥርዓት እስከዛሬ ድረስ ከ 12 ሺህ በላይ ነጋዴዎች ተመዝገበው በፍትሐዊ ውድድር እየተሳተፉ ይገኛሉ። በዚሁ ዘመናዊ ጨረታ ተመዝግበው ፤ ተወዳድረው ፤ አሸንፈው እና ውል ፈጽመው ግዴታቸውን እየተወጡ በፍትሀዊ መንገድ ተጠቃሚ መሆን እንደቻሉ የሚናገሩት ደግሞ የሸበሌ ጽዳት አገልግሎት ሰጪ ኩባንያ ሃላፊ አቶ አክሊል አወቀ ናቸው።

በመንግሥት በኩል እንዲህ በጉልህ የሚታዩ ነጋዴውን የሚያበረታቱ ስራዎች ሲከወኑ ምስጋና መቸር የቆየ ባሕላችን ነው። የተጀመረው መልካም አሰራር ይበል የሚያሰኝ ነው ነገር ግን። ይኸው መልካም ጅምር ዘላቂ ሆኖ እንዲቀጥል መንግሥት ከሥር ከሥር ክትትል እንዲያደርግ የብዙዎች አቅራቢዎች አሳስበዋል።

የመንግሥት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ሃጂ ኢብሣ በበኩላቸው በየአመቱ ከሚጸድቀው በጀት ላይ ከ65-70 በመቶ የሚሆነው ለግዢ የሚወጣ ነው ፤ ይህ ከፍተኛ ሃብት ለሙስና ክፍት ሆኖ ቆይቷል።

በዚህ አዲስ አሰራር ከመንግሥት በጀት ላይ እስከ 5በመቶ ወይም ወደ 40 ቢሊየን ብር ይድናል ይህም የአንድ ክልል በጀት ጋር ይስተካከላል ብለዋል።

አቶ ሃጂ እንደሚሉት ባለስልጣኑ በሚቀጥለው ዓመት ሙሉ በሙሉ የፌደራል መ/ቤቶች ወደ ኦንላይን ሥርዓቱ ይገባሉ፤በቀጣይም የክልል መ/ቤቶች እያለ በአገራችን ወጥ የመንግሥት ግዢ ሥርዓት እውን ማድረግ ጥረት የመ/ቤታቸው የቅርብ ጊዜ ህልም መሆኑን ተናግረዋል።

# መልካም ዜና

# ይማሩ! ይስሩ! ይበደሩ!

## አልፋ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ

ከ

## ኤዜድ ኢትዮጵ ትሬዲንግ አ.ማ

ጋር በመተባበር

## ለ500ሺ ሰልጣኞች የስራ እድል የሚያስገኝ

**የስልጠና መርሃግብር አዘጋጅቷል።**

ከ160 በላይ የስልጠና አይነቶች፣ ልዩ የክህሎት እና ልማድ ማጎልበት፣ በተግባር የተደገፈ ስልጠና ወስደው

**ወደ ስራ!**

ለሰለጠኑት ስልጠና የስራ እድል እና የብድር አቅርቦቶችን ያገኛሉ።

ለመሰልጠን እና የእድሉ ተጠቃሚ ለመሆን ይህንን QR Code ስካን በማድረግ ይመዝገቡ።

በየትኛውም ሙያ አሰልጣኝ ከሆኑ ይህንን QR Code ስካን በማድረግ ይመዝገቡ።

**ለበለጠ መረጃ +251 9 91 722 122 ወይም በድረ ገፅ www.alphareg.net ይጎብኙን።**

# አዲስ ቻምበር የአረንጓዴ ሽግግርን ፍኖተ ካርታ አስተዋወቀ





**በሰናይት እሸቱ**

ያለግሉ ዘርፍ ጠንካራ ተሳትፎ አረንጓዴ ሽግግርን ማሳካት እንደማይቻል ተጠቁሟል:: ምክር ቤቱ ከዳኒሽ ኮንፌዴሬሽን ኢንደስትሪ በተገኘ ድጋፍ አረንጓዴ ሽግግር ላይ ትኩረት በማድረግ ያስጠናውን ጥናት በባለሞያዎች አስተችቷል::

የአረንጓዴ ሽግግር ፍኖተ ካርታ የአየር ንብረት ለውጥ አለም አቀፍ አጀንዳ መሆኑን ተከትሎ ተጽኖው ኢትዮጵያን በመሰሉ ታዳጊ ሃገራት ላይም ከፍተኛ በመሆኑ ለማንቃት እና አቅጣጫ ለማሳየት ታሳቢ ተደርጎ የተዘጋጀ መሆኑ ተጠቁሟል:: የንግድ ስራ በተለመደው መልኩ ከቀጠለ ዘላቂነቱን ጥያቄ ውስጥ ስለሚከተው የአረንጓዴ ሽግግርን ታሳቢ ያደረገ የንግድ ስራ ትኩረት ያስፈልገዋል::

የኢኮኖሚ እድገት ከባቢ ሁኔታን በማጥፋት እና ማህበረሰብን ዋጋ በማስከፈል መምጣት የሌለበት በመሆኑ የኢኮኖሚ እድገት ከባቢ ሁኔታ እና ማህበረሰብ ተደጋግፎ እና ተጣጥሞ መሄድ መቻልም አለበትም ተብሏል::

ፍኖተ ካርታው 80 በመቶ የሚሆኑ የአዲስ አበባ እና በአካባቢዋ የሚገኙ ማህበረሰቦች እና የንግድ ስራዎች አረንጓዴ ሽግግርን ታሳቢ ያደረጉ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ማስቻልን ታሳቢ ያደረገ ሲሆን መንግስት እና የግሉ ዘርፍ በጋራ በመሆን አረንጓዴ ሽግግርን ታሳቢ ያደረጉ ፖሊሲዎች መዘጋጀት እንዲችሉ የሚያግዝ እና ከማህበረሰብ ጋር አብሮ ለመስራት የሚቻልበትንም መንገድ የሚያሳይ መሆኑ ተጠቁሟል::

የዜጎችን ኑሮ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሻገር የስራ እድል ለመፍጠር የግሉ ዘርፍ ሰፊ ድርሻ ያለው ከመሆኑ አንጻር በአረንጓዴ ሽግግር ዙርያ የተሻለግንዛቤ ኖሮት በእቅዶቻቸው ውስጥ ማካተት እንደሚያስፈልጋቸውም ተነስቷል::

ለዘላቂ ልማት የአየር ንብረት ለውጥ አንዱ ጉዳይ ሲሆን ሌሎች ተያያዥ ትኩረት የሚፈልጉ ማህበራዊ ሃላፊነትን መወጣት መልካም አስተዳደር እና ሌሎችንም የሚያቅፍ በመሆኑ ቀጣይነት ላለው ንግድ ስራ ሃላፊነት በተሞላበት መልኩ በማከናወን ተወዳዳሪ መሆን እንዲችሉ ግንዛቤ በመፍጠር ረገድ ንግድ ምክር ቤቱ ሃላፊነት እንዳለበት ተጠቁሟል::

ምክር ቤቱ ያዘጋጀው ፍኖተ ካርታም መነሻው በአዲስ አበባ ከተማ ይሁን እንጂ በሃገር አቀፍ ደረጃ የሚሰፋ መሆኑም ተብራርቷል::

# የምሥራች ለኩባንያ መሪዎች!!
# ከአዲስ ቻምበር የዳይሬክተሮች ተቋም



**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

የዛሬዋ ዓለማችን ከቀደሙት ጊዜያት ይልቅ ዛሬ ሩጫ የበዛባት፤ የበረታ ውድድር እና ፉክክር የምታስተናግድ ትልቅ ሁሉም የሚሮጥባት ሰፊ ገበያ እየሆነች መጥታለች ብንል ብዙዎችን የሚያስማማ ይመስላል:: በተለይ አንደ እንዝርት የሚሾረው የዓለም ንግድ እንቅስቃሴ ዋናው ዘዋሪ የመረጃ ተክኖሎጂ አብዮት ነው ሲሉ አዋቂዎች ይናገራሉ:: በየቀኑ በዓለም ገበያ በትሪሊየን የሚቆጠሩ ዶላሮች ይገለባበጣሉ-፤ ምርት እና አገልግሎቶች ይሸጣሉ፤ ገንዘቦች ይመነዘራሉ::

በሰከንድ ከአንድ ቀበሌ የተመረተ በቅጽበት አራቱንም የዓለም ማዕዘናት ላይ ለገበያ በሚሰደርበት ሰፊ ሜዳ ላይ የግሉ ዘርፍ ዋናው ተወናይ ነው:: ስለዚህ የአገራችን ነጋዴዎች በዚያ ፍጥነት ልክ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት ዘመናዊ እና ቀልጣፈ የንግድ ዘርፍ መገንባት የግድ ያስፈልገናል:: በሌላ አነጋገር ያገራችን የንግድ ድርጅቶች በተለይ በባለሃብቶች አክሲዮን የተቋቋሙ ትላልቅ ኩባንያዎች ለአህጉራዊም ይሁን ዓለማቀፋዊ የገበያ ውድድር አስቀድመው መዘጋጀት ይጠበቅባዋል:: የእነዚህ የቢዝነስ ተቋማት ታዲያ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመዝለቅ ዕለት ተለት የሚያንቀሳቅሷቸውን መሪዎችን ብቁ የቢዝነስ መሪዎች አድርጎ ማብቃት ዋናው እና ትልቁ ሥራ ነው:: በተለይ የቦርድ አባለት፤ፕሬዝደነቶች፤ የኩባንያ ሥራ አስፈጻሚዎች ዳይሬክተሮች ያሉ ብዙ ሠራተኞችን የሚያስተዳድሩ እና ትልልቅ የሕዝብ ሃብት ላይ ውሳኔ የሚያሳልፉ ሰዎችን አቅም ማሳደግ አገራዊ ጥቅሙ የበዛ ነው::

ይህንን ትልቅ ትርጉም ያለው እና ፋይዳው ከንግዱ ሕ/ብ አልፎ አገራዊ ተወዳዳሪነትን ሊያሳድግ የሚችል ትልቅ ተግባር አስቀድሞ በማሰብ የአዲስ አባበ ንግድ ም/ቤት በቅርቡ Institute of Directors / የዳሬክተሮች ተቋም የተባለ አዲስ ለከፍተኛ የቢዝነስ መሪዎች የስልጠና አገልግሎት በይፋ አስጀምሯል:: የዚህ ጽሑፍ ዓላማም ስለዚሁ ተቋም ለክቡራን እና ክቡራት አንባቢያት ከብዙ በጥቂቱ ማስተዋወቅ ይሆናል::

የአዲስ ቻምበር የዳይሬክተሮች ተቋም በዋናነት የኩባንያዎችን ዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትና አመራሮችን በኩባንያ መልካም አስተዳደር እና በአመራር ረገድ አቅም የሚያጎለብት ትልቅ ማዕከል እንደሚሆን ይጠበቃል:: እኛ የመጀመሪያ በሆነው ስልጠና ላይ ያገኘናቸውን የኩባንያ መሪዎች ስለስልጠናው የነገሩንን እና የምክር ቤቱ መሪዎች የሰጡንን ማብራሪያ እንደሚከተለው አሳጥረን አቅርበናል::

**ይህ የዳይሬክተሮች ተቋም በአገራችን ኩባንያዎች ዘንድ ሃላፊነት እና ተጠያቂነት አንዲሁም ግልጽ አሰራር የሚታይበት ወጥ የሆነ የኮርፖሬት አመራር ለማምጣት ወሳኝ ተቋም ነው። ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ (የአዲስ ቻምበር ፕሬዝደንት)**

ንግድ ም/ቤታችን የነጋዴው ድምጽ መሆን ብቻ ሳይሆን ፤የም/ቤቱ አባላት በራሳቸው ቢዝነሶቻቸውን ጤናማ በሆነ መልኩ ሲመሩ ብቻ ውጤታማ እንደሚሆኑ ያውቃሉ:: የም/ቤታችን አንዱ ርዕይ አንዱ ዘመኑ የሚጠይቀውን ንግድ አሰራር፤ስብዕና ስነምግባር የተላበሱ አባላትን ማፍራት ነው:: አባላቶቻችን ትክለኛውን እና ዘመኑ የሚጠይቀውን የንግድ ሰብዕና አንዲላበሱ፤የኩባንያ መሪዎች ደግሞ የሚመሩትን ቢዝነስ በእውቀት፤በክህሎት እና በመልካም የኩባያ አመራር መርሆች ባሕል አንዲያደርጉ ድጋፍ ማድረግ ነው:: ስለዚህ ይህ የዳይሬክተሮች ተቋም በአገራችን ኩባንያዎች ዘንድ ሃላፊነት እና ተጠያቂነት አንዲሁም ግልጽ አሰራር የሚታይበት ወጥ የሆነ የኮርፖሬት አመራር ለማምጣት ወሳኝ ተቋም ነው::

የተቋሙ ዓላማም ሆነ የሚሰጣቸው ስልጠናዎች የአንድ የቢዝነስ ድርጅት ሕልውና መትጋት ነው:: የአንድ ኩባንያ ዘላቂነቱ ደግሞ በቦርድ አባላት፤በማኔጅመንቱ እና በሠራተኞች ትከሻ ላይ ያርፋል:: ነገር ግን ከፍተኛ መሪዎች (የቦርድ አባላት እና ሥራ አስፈጻሚዎች) የኮርፖሬት አስተዳደር የሰፈነበት፤ደህንነቱ የተጠበቀ፤ የጥቅም ግጭት የሌለበት ሥራ እና ውጤት ለማምጣት ማሰብ፤በአመራሩ ሥራ ላይ አለመግባባት የመሳሰሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ:: በአጠቃላይ የኩባንያውን ሕልውና ይዘው ወደ ስኬት የሚጓዙ ዳይሬክተሮች መሆን አለባቸው:: ለምሳሌ የአክሲዮን ኩባንያዎችን እናንሳ:: በእኔ እምነት ከአክሲዮን ኩባንያዎች መካከል ባንኮች እና መድን ሰጪ ኩባያዎች ስኬታማዎች ናቸው:: ለምን ቢባል በእነዚህ ትላልቅ ድርጅቶች ኮርፖሬት ገቨርናንስ መርሆዎችን ይከተላሉ:: ሌሎቹ አብዛኛውን ጊዜ በአንድም በሌላ መንገድ ይከስማሉ፤ወይም ደግሞ ወደ ሌላ ንግድ ዘርፍ ይገባሉ፤ ብቻ በተለይዩ ምክንያቶች ሕልውናቸው አጭር ነው:: ስለዚህ በአገር ደረጃ ትክለኛውን የኩባንያ አመራር ባህል መከተል አለብን:: በተለይ የባላአክሲዮኖች ሃብት አያያዝ፤የቁጥጥር ስርዓቱ፤ አንዲሁም አብዛኞቹ ዳይሬከተሮች ትክክለኛውን እና ዘመናዊ የኩባንያ አመራር ባለመከተላቸው ለውጤት አይበቁም:: ለዚህም ዋናው ምክንያት በሕዝብ ሃብት የሚቋቋሙ ኩባንያዎችን የሚመሩ ዳይሬክተሮች በእውቀት፤በክህሎት እና በስብዕና ብቁ አድርጎ የሚያወጣ የሥልጠና ተቋም ባለመኖሩ ነው:: ስለዚህ ንግድ ም/ቤታቸን ይህንን ክፍተት ለመሙላት የዳይሬክተሮች ተቋም በይፋ አስጀምሯል:: አባሎቻችንም ሆኑ መላው የአገራችን ኩባንያዎች በዕድሉ አንዲጠቀሙ ጥሪ አቀርባለሁ::

**ተቋሙ የግሉን ዘርፍ ከውስጡ ለመቀየር ያችላል።**
**(አቶ ሺበሺ ቤተማርያም የአዲስ ቻምበር ዋና ፀሐፊ)**

የዳይሬክተሮች ተቋም በአውሮጳ የረዥም አመታት ታሪክ አለው:: በተለይ በብሪታንያ አንደ እ.ኤ.አ በ1906 አንደመጀመሩ የአገሪቱ ኩባያዎች በዘላቂነት አንዲያድጉ ተቋሙ ትልቅ አስተዋጽኦ ነበረው:: ዛሬ የብዙ አገራት የዳይደሬክሮች ተቋማት መነሻ ለመሆን ችሏል:: የኛ ዋና ዓለማ ዳይሬክተሮችን ማብቃት ነው:: የኩባንያ መሪዎችን በተለያዩ ሙያዎች በማገዝ ሙያዊ ብቃት/professionalize/ አንዲያገኙ ማገዝ ነው::

ዛሬ በዓለም ላይ ዳይሬክተሮች በቀላሉ የሚገኙ ባለሙያዎች አይደሉም:: የአንድ ሙያ ባለቤት ሊሆኑ ይችላሉ:: ነገር ግን የኩባንያ ዳይሬክተር መሆን ሌላ ሙያ ነው:: ለምሳሌ አንድ በዓለም ላይ ባሉ ትላልቅ የቢዝነስ ኩባንያዎችን የሚመሩ ብቃቱ ያላቸው የአገሬው ዜጋ ላይሆኑ ይችላሉ:: ለምሳሌ በአንድ የደቡብ አፍሪቃ ኩባንያ ውስጥ አንድ የካናዳ ዜጋ የቦርድ ዳይሬክተር ሆኖ ሊያገለግል አልያም አንድ ደቡብ አፍሪቃዊ ባለሙያ ዳይሬክተር በእንግሊዝ በሚገኝ ግዙፍ ኩባያዎች ዳይሬክተር ሆኖ ሲያገለግል ልናይ አንችላለን:: ይህ በዓለም የተለመደ አሰራር ነው:: በእኛ አገር ግን ዳይሬክተር መሆን በሙያ የታገዘ አይደለም::

ይህንን የኮርፖሬት አመራር ባሕል ክፍተት በተቻለ መጠን ለመሙላት ንግድ ም/ቤታችን ቀደም ሲል የኮርፖሬት ሥራዎችን ይሰራ ነበር:: የንግድ ም/ቤታችን ዋና ዋና ሥራዎች 3 ናቸው:: 1ኛው ንግድልማት ሲሆን 2ኛው የፖሊሲ አድቮከሲ ነው:: 3ኛው እና ዋነኛው የግሉን ዘርፍ ከውስጡ መቀየር ናቸው ማለት ይቻላል:: የግሉን ዘርፍ ከውስጡ በመቀየር ከዓለምአቀፋዊ ሁኔታዎች ጋራ የተገናዘበ ፣ተወዳዳሪ የሆነ ኩባንያ አድርጎ መፍጠር አንደማለት ነው::

የኮርፖሬት ገቨርናንስ ዋና ዕሳቤው በኩባንዎች ባለቤቶች እና ኩባያዎቹን በሚመሩ መሪዎች መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው:: የጥቅም ግጭቶች እና ሌሎች አለመግባባቶች ቢኖሩ እንኳን ለመፍታት ያስችላል:: የዳይሬክተሮች ተቋም ስንጀምር የታሰበለትን ትልቅ ተልዕኮ እንዲወጣ አንደ ቻምበር ባለድርሻዎችን ታሳቢ አድርገናል:: ለምሳሌ የኢትዮጵያ ኦዲት እና አካውንቲንግ ቦርድ፣ ብሄራዊ ባንክ፣ በቀር የተቋቋመው የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን አለ:: እነዚህ ተቋማት ያገራችንን ዳይሬክተሮችን ቅርጽ ይወስናሉ:: ያገራችን ዳይሬክተሮች ብዙ ኃላፊነት አለባቸው:: በቢሊየን የመቆጠሩ ሃብቶች ላይ የሚወስኑ ናቸው:: የአገር ሃብት የሚያንቀሳቅሱ ናቸው እነዚህ ሰዎች ሊታገዙ ይገባል:: እነዚህ ሰዎች ግልጽነት፣ እና ተጠያቂነት ባለው ተቋማዊ አሰራር ሊየጠቁ ይገባል:: የዳይሬክተሮች ተቋም ማለት የሚሰራው አንዱ ይሄንን ነው::

**ብዙ የተማሩ ሰዎች አሉን.... ተማሩ ማለት የመሪነት ብቃት አላቸው ማለት አይደለም::**
**አቶ ኤልያስ ገነቲ (የአዋሽ ባንክ የቦርድ አባል)**

የዳይሬከተሮች ስልጠና እጅግ በጣም አስፈላጊ ሆኖ አግኝቸዋለሁ:: ይህን የምልበት በሁለት ምክንያት ነው:: የመጀመሪያው ጊዜ ተለዋዋጭ ነው:: በዚያው ልክ እወቀትም እየተለዋወጠ ነው የሚሄደው:: በተለይ አሁን በዚህ ጊዜ የአመራር ብቃት ዓለማቀፋዊ ይዘት ያለው ነው:: መሪዎች የተለያዩ ዕውቀቶች ባለቤት እንዲሆኑ የሚፈለግበት ዘመን ነው:: ያገራችንን ከውጪ ልምድ መውሰድ ነገር ስናየው ብዙ ይቀረናል:: ስለዚህ ንግድ ም/ቤቱ ይህንን በማሰብ የአዲስ የኩባንያ አመራር መሰረት ለመጣል ላደረገው ጥረት ለማመስገን እወዳለሁ:: 2ኛ እኔ ከፋይናነስ ዘርፍ ነው የመጣሁት መንግሥት ለውጪ ኩባንያዎች ዝግ ሆኖ የቆየውን የፋይናንስ ዘርፍ ክፍት ለማድረግ ከወሰነ ቆይቷል:: ስለዚህ የውጪ የፋይናንስ ተቋማት መምጣታቸው አይቀርም:: ስለዚህ ለሚገጥመን ጠንካራ ፉክክር ብቁ የፋይናንስ መሪዎች ያስፈልጉናል:: አለበለዚያ ያገራችን ፋይናንስ ተቋማት ከውጪ በሚመጡት ሊዋጡ ይችላሉ:: የቢዝነስ አመራር ባሕላችን ሊቀየር ይገባል:: በብዙ መልኩ ኋላ ቀር ነው:: አንዲህ ባለ ሁኔታ ለውጪ ገበያ ኢኮኖሚያችንን ክፍት ማድረግ የራሱ ስጋቶች አሉት:: ስለዚህ የቢዝነስ ዘርፉን ለማዘመን እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ብቁ ዳይሬክተሮች ያስፈልጉናል:: ለዚህ ደግሞ የአዲስ ቻምበር የዳይሬክተሮች ተቋም ጥቅሙ የበዛ ነው:: ብዙ የተማሩ ሰዎች አሉን:: ነገር ግን ተማሩ ማለት የመሪነት ብቃት አላቸው ማለት አይደለም:: የመሪነት ብቃት በብዙ መልኩ የሚመጣ ነው:: የመሪነት ችሎታ ከትምህርት ሊመጣ ይችላል፣ከልምድ ሊገኝ ይችላል፣ በተጨማሪ ደግሞ እንደዚህ ካሉት ተቋማት ነው::

**ሰዎችን ማዘዝ ማለት መሪ አያስብልም ...ይልቅ ሰዎች አንዲሰሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይቀድማል።**
**አቶ ሰመረ አክሊሉ (ከማይዊሽ ኩባንያ)**

ስልጠናው ጥሩ ሆኖ አግኝቸዋለው:: በዚህ ስልጠና መሪነት ማለት አንደተለመደው ማዘዝ፣አንተ እንዲህ አድርግ አንተ ደግሞ ያንን ሥራ ማለት እንዳልሆነ ተገንዝቤአለሁ:: መሪነት ከዚህ የተለየ ነው የራሱ ሳይንስ አለው:: የአለቅነት ባሕላችንን መቀየር አለብን እላለሁ:: ከስልጠናው ያገኘሁት ሌላው ጥሩ ማናጀሮች ሊኖሩ ይችላሉ:: መሪ ማለት ከሠራተኞች አብልጦ እና አስፍቶ ወደፊቱን የሚያይ፣የሚመራውን ኩባንያ ቀዳዳዎችን እና ሊመጡ የሚችሉ ስጋቶችን አስቀድሞ ማሰብ፣መተንተን እና መዘጋጀት አለበት:: መምራት ማለት ለሰዎች አንዲሰሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ማለት ነው:: ሁሉም ኩባንያዎች መሪዎቻቸውን ወደዚህ ተቋም መላክ አለባቸው:: ከዚህ ብዙ እውቀቶች፣መሪነት ብልሃቶች እና ጠቃሚ ቁምነገሮችን ያገኛሉ::

# የታዳሽ ሀይል አቅርቦት ለአፍሪቃ...

**ከ ገጽ 3 የዞረ**

ዘገባዎች እንደሚያመላክቱት የሰሜን አፈሪቃዊቷ ሀገር ግብጽ ታዳሽ ሀይልን በመጠቀም የህዝቦቿን የኤልክትሪክ ፍጆታ ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ መመለስ ችላለች:: ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ የታዳሽ ሀይል እምቅ ሀብት ያላት ኢትዮጵያ ከግማሽ በመቶ ያህል ህዝቦቿ የኤልክትሪክ አገልግሎት ማግኘት እንደተሳናቸው መረጃዎች ያሳያሉ::

ስለሆነም ዜጎች የሀይል ፍላጎታቸውን ለመመለስ ወደ ደን ምንጠራ በመግባት የአለም ሙቀት እንዲጨምር በስነ ምህዳር ላይ የሚደርሰው ጫና ከፍ እንዲል ሆኗል:: የ2022 የኢነርጂ አውትሉክ የኢትዮጵያ ሪፖርት እንደሚያሳየው ከሆነ 86 በመቶ የሀገሪቱ የሀይል ፍላጎት ምንጭ ባዮ ማስ ወይም ከደን የሚገኝ እንደሆነ ነው:: የተባበሩት መንግስታት የዘለቂ ልማት ግብ 7 እ.አ.አ በ2030 በዋጋ ቅናሽ ያለው እና ተደራሽነት ያለው የኤልክትሪክ ሀይል ፍጆታ በአለምአቀፍ ደረጃ ተደራሽ እንዲሆን ይሻል::

የተባበሩት መንግስታት የዘለቂ ልማት ግቦች አስተማማኝና ዘመናዊ የታዳሽ ሀይል አቅርቦት ሆኖ እንዲዘልቅ በግብነት ተይዟል:: እንደ ፓን አፍሪቃ ክላይሜት ጀስቲስ አልያንስ የቅርብ ሪፖርት በአፈሪቃ የሀይል ፍላጎት አሁን ካለበት እ.አ.አ በ2040 በእጥፍ እንደሚድግ ይገምታል:: ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር መጨመርና የዘመናዊ አኗኗር እያደገ መምጣት የኤክትሪክ ፍላጎትን ከፍ እንዲል አይነተኛ ሚናን ይጫወታሉ::

በርካታ የተፈጥሮ ሀብት ያላት አፍሪቃ በእርግጥ የማደግ ተስፋዋ ከፍተኛ ሲሆን ይህ ሁለንተናዊ እድገት ዘላቂ የልማት ግቦችን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት በማለት በርካታ ምሁራን ሀሳባቸውን ይሰነዝራሉ:: እነዚህ ምሁራን አክለው ሲገልጹ አፍሪቃ የምትከተለው የልማት መስመር የዘላቂ ልማት አስተሳሰቦችን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት በማለት በርካቶች ይሞግታሉ::

በእርግጥ በአፍሪቃ ሆነ በኢትዮጵያ የታዳሽ ሀይል ልማትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት በብዙ ውዝግቦች የታጀበ እንደሆነ ይነገራል:: ወደ ታዳሽ ሀይል የሚደረገው ጉዞ በእውቀትና በቴክኖሎጂ ብቻ ሳይሆን በከፍተኛ ፋይናንስም መሆን አለበት በማለት በርካታ ምሁነራን ሀሳባቸውን ያጋራሉ:: እንደ ሶላር ፣የውሀ ሀይል ማመንጫ ግድቦች፣ ጂኦተርማልና የንፋስ ሀይል መሰረተ ልማቶችን በስፋት ለማልማት ከተፈለገ እንደ ኢትዮጵያ የመሳሰሉ የአፍሪቃ ሀገራትን በፋይናንስ በመደገፍ አንድም ድህነትን መቀነስ የሚቻል ሲሆን በሌላ መኩል ደግሞ የአለም የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ጉዳት ለመከላከል ይረዳል:: በተለይም የታዳሽ ሀይል ልማትን በኢትዮያም ሆነ በሌሎች የአፍሪቃ ሀገራት ተግባራዊ ማድረግ ፋይዳው ዘርፈ ብዙ ነው:: የታዳሽ ሀይል ልማት ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ማደግ ለስራ እድል ፈጠራ እንዲሁም ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ በር ይከፍታል:: የታዳሽ ሀይል አቅርቦት ማህበረሰብ በቀላሉ የኤልክትሪክ አገልግሎት እንዲያገኝ እና የስራ እድሎች እንዲፈተሩ ያደርጋል::

እንደ ኢትዮጵያ የመሳሰሉ የአፍሪቃ ሀገራት ለታዳሽ ሀይል ልማት በተለይም የታላቁን የህዳሴ ግድብ ለመገንባት የውጭ ሀገር ብድርና እርዳታ ለማግኘት ተጽእኖ መበርታቱ የሀገሬው ሰው በራሱ እውቀትና ገንዘብ ግድቡን እንዲገነባ አስችሎታል::

በቀጣይ ለሚደረጉ የታዳሽ ሀይል ልማቶች እንደ IMF እና WB የመሳሰሉ ተቋማት እንደዚህ አይነት ሀገራትን በፋይናነስ የመደገፍ ሀላፊነት አለባቸው:: እስከዛው ግን ኢትዮጵያ በታዳሽ ሀይል ኢንቨስትመንት መሰማራት የሚፈልጉ የውጭ ሀገር ባለ ሀብቶችን ለመሳብ የሚያስችል የኢንቨስትመንት መስህቦችን መፍጠር አለባት:: በተለይም ደግሞ ኢትዮጵያ ያላትን እምቅ ታዳሽ ሀይል ለውጭው አለም በማስተዋወቅ ከፍተኛ ስራን መስራት ይጠበቅባታል:: የኢትዮጵያ መንግስት እ.አ.አ በ2030 ሁለም የሀገሪቱ ክፍሎች የኤሌክትሪክ አቅርቦት እንዲዳረስ በመስራት ላይ ይገኛል:: ነገር ግን ይህን ግብ ለማሳከት መንግስት ከግሉ ዘርፍ ጋር ተቀራርቦ በመስራት የግሉ ዘርፍ በታዳሽ ሀይል ኢንቨስትመንት በስፋት እንዲሰማራ ማድረግ አለበት:: ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ አመቺ የኢነርጂ ፖሊሲዎች እና አሰራሮች እውን እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል:: ይህ ተግባራዊ የሚደረግ ከሆነ በርካታ የታዳሽ ሀይል ፕሮጀክቶችን በኢትዮጵያ ማየት የሚቻል ሲሆን ዜጎች በቅናሽ ዋጋ አስተማማኝ የሀይል አቅርቦት እንዲያገኙ በር ይከፍታል:: አስተማማኝ የሀይል አቅርቦት ዜጎች የስራ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ፣ስራ ፈጣሪዎች እንዲሆኑና ለሀገር እድገት አስተዋጾ እንዲያደርጉ በር ይከፍታል::

በፋይናንስ ረገድ በቅርቡ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የወሰደው እርምጃ ይበል የሚሰኝ ነው:: ይህ ውሳኔ በታዳሽ ሀይል ለመሰማራት ለሚፈልጉ የውጭ ሀገር አልሚዎች የባንክ ዋስትና ለመስጠት የተወሰደ እርምጃ በርካታ የውጭ አልሚዎችን በታዳሽ ሀይል እንዲሰማሩ የሚያበረታታ እንደሆነ ይታመናል::

# የቤት ግብር ተመን ማሻሻያው በአተገባበሩ ላይ ክፍተቶች እንዳሉበት የንግዱ ማህበረሰብ አባላት ገለጹ...

ከ ገጽ 1 የዞረ




የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ አቶ አደም ኑሪ ለውይይቱ ተሳታፊዎች ባቀረቡት ገለፃ እየተገለገልነበት ያለው አዋጅ በ1968 ዓ.ም የወጣውና አዋጅ ቁጥር 80 በመባል የሚታወቀው የከተማ ቦታ ኪራይና የቤት ግብር በመባል የሚታወቀው እንደነበር ጠቅሰዋል። ነገር ግን ከተማዋ ቀድሞ ያልነበሩ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ፣ ቪላ ቤቶችና ሪል ስቴቶች ጋር በተያየዘ አዋጁ በክፍያው ላይ ወቅታዊ በማድረግ ረገድ ክፍተት ያለበት መሆኑን አንስተዋል። ይህም ከከተማዋ እድገትና አሁን ካለንበነት የመሰረተ ልማት ፍላጎትና እድገት ደረጃ ጋር አብሮ የሚራመድ ግብር መሰብሰብ አልተቻለም ያሉት አቶ አደም በዚህም ምክንያት በከተማዋ ማህበረ-ኢኮኖሚ መሰረተ ልማትን ማስፋፋት ላይ ውስንነት እንዲኖር አድርጓል ብለዋል። አክለውም በቀድሞው አዋጅ ‹‹የጣሪያና የግድግዳ ግብር ከሚከፍሉ የከተማዋ ነዋሪዎች መካከል 96 በመቶ የሚሆኑት ከአምስት መቶ ብር በታች ይከፍሉ ነበር ›› ብለዋል። ይህም ገንዘብ ለልማት ሊውል ቀርቶ የመሰብሰቢያንም ወጭ የሚሸፍን አልነበረም ሲሉ ግለፀዋል።

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ወ/ ሮ መሰንበት ሸንቁጤ ግብር ለከተሞች እድገት የጀርባ አጥንት መሆኑን ጠቅሰዋል። ሆኖም በግብር ዙሪያ የሚወጡ አዋጆችና ደንቦች ከመውጣታቸው በፊትም ሆነ ከወጡ በኃላ የሚመለከታቸውን አካላት ሲያሳተፉ አይታይም ያሉት ወ/ሮ መሰንበት ከዚህ አንፃር ክፍተት እንዳለ አንሰተዋል። በመሆኑም ንግድ ምክር ቤታቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በማመቻቸት መንግስትና የግሉ ዘርፍ ቀርበው እንዲመክሩ መድረክ ማዘጋጀቱን ገልፀዋል።

ይህም በግብር ጉዳዮች ላይ መተማመን እንዲኖር እና ችግሮችም ካሉ ለመቅረፍ መንግስት የሚጠበቅበትን ገቢ እንዲሰበስብ ያስችላል ብለዋል። የአዲስ አበባ የንብረት ግብር ማስተባበሪያ ፅ/ቤት ኃላፊ አቶ አስማማው ሙሉጌታ በበኩላቸው የቤት ግብር አከፋፋል ላይ እሴትን ያገናዘበ ሆነ እንጂ አዲስ አዋጅ አልወጣም ብለዋል።

በከተማዋ ከ285 ሺ. በላይ ግብር ከፋዮች እንዳሉ ጠቅሰው ከተማዋ የምትሰበሰበው ግብር ከሌሎች አገራት ጋር ሲነፃፀር አነሰተኛ መሆኑን ገልፀዋል። ናይሮቢ ከአጠቃላይ ግብር ውስጥ የቤት ግብር 20 በመቶ ሲሆን ፣ የዛምቢያዋ ዋና ከተማ ሉሳካ 74 በመቶ እንደሚሰበሰቡ ለማሳያነት አቅርበዋል። ይሁንና አዲስ አበባ ከተማ የምትሰበስበው ከ1 በመቶ በታች 0 .08 መሆኑን አንስተዋል።

የአዲስ ቻምበር የግልግል ተቋም ዳይሬክተር አቶ ዮሀንስ ወ/ ገብርኤል ባቀረቡት የህግ ምልከታ በአዋጅ የወጣ የግብር ተመን ማሻሻያ የሚሻሻለው በአዋጅ ነው ሲሉ ሞግተዋል። በህግ የወጣ የግብር ተመን ማሻሻያ የሚሻሻለው በህግ ነው። አዲስ ደንብም ሲወጣ በደንብ ይተካል ሲሉ አክለዋል። የኢንቨስትመንት አማካሪው አቶ ያሬድ ሀይለ መስቀል በበኩላቸው ይህ የቤት ግብር ተመን ማሻሻያ ወቅቱን ያላገናዘበ እና ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ሊያስከትል የሚችል ነው ሲሉ ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮ አንጻር ሞግተዋል።

በውይይቱ ላይ ተሳታፊ የነበሩ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት በበኩላቸው ግብር መክፍሉን አንደግፋለን ነገር ግን አሁን ያለውን የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ታሳቢ ያደረገ አይደለም ሲሉ ተደምጠዋል። በተጨማሪም የመክፍል አቅም የሌላቸው ዜጎች መክፍል አይችሉም እና እነርሱስ እንዴት ይታያሉ የሚሉ ጥያቄዎች ከተሳታፊዎች ተነስተዋል። ህብረተሰቡ ላይ ተደራራቢ ችግር እንዳለ እንረዳለን ያሉት አቶ አስማማው ሆኖም የቤት ግብር ትመናው በጥናት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ጠቅሰው የመክፍል አቅም የሌላቸው ባለቤቶች መክፍል እንደማይችሉ ከተረጋገጠ ለአንድ አመት ከከፍያ ነፃ የሚሆኑበት አሰራር መዘርጋቱን አስታውቀዋል።

የአምልኮ ቦታዎች ፣ ኢምባሲዎች ፣ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የቤት ግብር ማሻሻያው የማይመለከታቸው መሆናቸውን የንብረት ግብር ማስተባባሪያ ፅህፈት ቤቱ አስታውቋል። በመጨረሻም ምክር ቤቱ እንዲህ አይነቱን የአድቮኬሲ የምክክር መድረክ በቀጣይ ጊዜያትና በወቀቱ ለአባላቱ የሚያዘጋጅ እንደሆነ ገልጿል።



# Addis Chamber Training Institute (ACTI)

## List of July & August 2023 Training Programs

| No. | Training Topic | Delivery Date | Time | Training Fee | | Venue | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | Member | Non-Member. | | |
| 1 | Advanced Customer Service | July 24-28, 2023 | 8:30AM - 12:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 2 | International Trade Service & Ethiopian Export/Import Practice | July 31 - Aug. 4, 2023 | 8:30AM - 12:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 3 | Salesmanship | July 31 - Aug. 4, 2023 | 1:30P.M-5:30P.M | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 4 | International Financial Reporting Standards (IFRS) | August 7-25, 2023 | 8:30AM - 12:30PM | 8,625 | 10,350 | ACTI | 15 half days |
| 5 | Basic Managerial skills | August 7-11, 2023 | 1:30P.M-5:30P.M | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 6 | Records Management | Aug. 28-Sept. 1, 2023 | 8:30AM - 12:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 7 | Office Operations Management | Aug. 28-Sept. 1, 2023 | 1:30P.M-5:30P.M | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 8 | Leadership Skills | August 1-2, 23 | 8:30A.M -5:30 P.M | 5,929 | 7,115 | Hotel | 2 full days |
| 9 | Stores Management | August 14-18, 2023 | 8:30AM - 12:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 10 | Transformational Leadership | August 15-17, 2023 | 8:30A.M -5:30 P.M | 8,591 | 10,309 | Hotel | 3 full days |
| 11 | Project Management | August 21-25, 2023 | 8:30AM - 12:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |

**For further information, please contact the Training Institute through 011-551-3882, 011-551-8055 ext. 229, 0911194965, 0911343078, dejedesalegn@gmail.com and hiwottlhn9@gmail.com**

# በኢትዮጵያ የዲጅታል ቴክኖሎጅ አማካይነት የሚካሄድ ግብይት በአውሮፓዊያኑ አቆጣጠር በ2025 ስልሳ ቢሊየን ዶላር ይደርሳል ተባለ




**በከፍያለው ዋሲሁን**

በዲጅታል ቴክኖሎጅ አማካይነት የሚደርግ ግብይት ከኢትዮጵያ ጥቅል አመታዊ ምርት ( ጂዲፒ) 39 በመቶ አበርክቶ እንደሚኖረውም የቻፓ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ መስራችና ስራ አስኪያጅ አቶ ናይል ኃ/ ማርያም ገልፀዋል፡፡
አዲስ ቻምበር ‹ ዲጅታል ቴክኖሎጅ ውጤቶች በቢዝነስ ልማትና ፈጠራ ያላቸው እንድምታና ተፅዕኖው › በሚል ርዕስ በቅርቡ ባዘጋጀው የቻምበር ፎረም ላይ ማብራሪያ የሰጡት አቶ ናኤል ፤በኢትዮጵያ የዲጅታል ግብይት ጅምር ላይ መሆኑን ጠቅሰው ፤ ዲጅታል ቴክኖሎጅን በሀገር አቀፍ ደረጃ ማስፋፋት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡
ኢትዮጵያ ከአጠቃላይ ምርቷ ውስጥ 60 በመቶ የሚሆነው የሚገኘው ከግብርና መሆኑን ያነሱት አቶ ናይል አርሶ አደሩን ዲጅታል ቴክኖሎጅን ተጠቃሚ ለማድረግ ወደ ገጠር ማስፋት ያስፈልጋል ሲሉ ገልፀዋል፡፡ ዲጅታል እውቀትን በተመለከተ ብዙም ያደገ አለመሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በኢትዮጵያ ካለው 120 ሚሊየን ህዝብ ውስጥ 6 ሚሊየን ህዝብ ነው ማህበራዊ ሚዲያን እንደሚጠቀም ለማሳያነት አቅርበዋል፡፡ ጅምሮች ጥሩ ቢሆንም ዲጅታል ቴክኖሎጅን ተጠቅሞ ግብይት መፈፀም ላይ በአንፃራዊነት በከተማ የተሸለ ቢሆንም ፤ በአነስተኛ ቢዝነስ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ከፍተኛ ቁጥር እንደሚይዙ ጠቁመው ፤ እነዚህን ድርጅቶች ወደ ዲጅታል ቢዝነስ ማምጣት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የሚልኩት ገንዘብ በባንክና በጥቁር ገበያ ምንዛሬው የተለያየ መሆኑ በባንክ በኩል ወደ ኢትዮጵያ የሚላከው ምንዛሬ አነስተኛ ነው ብለዋል፡፡
ለአብነት የባለፈውን የአወሮፓዊያንን 2022 ያነሱት አቶ ናኤል በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በባንክ ወደ ሀገራቸው የላኩት ገንዘብ 4 ቢሊየን ዶላር ነበር ብለዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ የጥቁር ገቢያውን ለማስቀረት ገቢያው እንደሚራው ማድረግ ትልቅ ጥቅም ስለሚኖረው ወደ አገር ውስጥ የሚላከውን ገንዘብ እስከ 20 ቢሊየን ዶላር ማድረስ እንደሚቻል ገልፀዋል፡፡ የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ( አዲስ ቻምበር ) ምክትል ዋና ፀሀፊ አቶ ዘካሪያስ አስፋ በበኩላቸው የዲጅታል ቴክኖሎጅው እያደገ እና መሻሻል እያሳየ መሆኑን ጠቁመው፤ የቴክኖሎጅ ተጠቃሚዎችን ቁጥር ማሳደግ ያስፍልጋል ብለዋል፡፡

ያለ ቴክኖሎጅ የቢዝነስ ስራ ፈጠራ ብዙ ሊራመድ አንደማይችል ጠቅሰው ቢዝነስ ዘመኑን የዋጀ እንዲሆን በቴክኖሎጅው ልንደግፈው ይገባል ብለዋል፡፡

# የአፍሪቃ ሀገራት መሪዎች በታዳሽ ሀይል እና በውሀ መሰረተ ልማት የሚደረገውን ኢንቨስትመንት እንዲስፋፉ በማድረግ የዘላቂ ልማት ግቦች በፍጥነት እንዲሳኩ ጥሪ አቀረቡ



(ኔውዮርክ ሀምሌ 12 2015 አ.ም ኢሲኤ) በኒውዮርክ የአፍሪቃ መሪዎች የተቀናጀ የሀይልና የውሀ መሰረተ ልማት ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ በማድረግ የተባበሩት መንግስታት የዘላቂ ልማት ግቦች በፍጥነት እንዲሳኩ እና የአፍሪቃ የ2063 አጀንዳ እውን እንዲሆን ጥሪ አቀረቡ፡፡

የአፍሪቃ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ተጠባባቂ ዋና ጸሀፊ የሆኑት አንቶኒ ፔድሮ በኒውዮርክ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር የአፍሪቃ ልማትን በተመለከተ በጥልቀት ማሰብ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የአፍሪቃ ልማት የአየር ንብረት ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት መቋቋም የሚችል መሆን አለበት ብለዋል፡፡

ይህ የልማት ሽግግር ፍትሀዊ፤ ሰዎችን ማእከል ያደረገ፤ አካታችና አፍሪቃ የቀረጸችውን የልማት አጀንዳ ከግምት ውስጥ የሚከት መሆን አለበት ብለዋል፡፡

በኒውዮርክ በተካሄደው የአፍሪቃ ቀን ዘላቂ የኢንዱስትሪና አካታች የኢኮኖሚ ሽግግር በሚል መሪ ቃል የተካሄደው ጉባኤ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፤የተባበሩት መንግስታት የአፍሪቃ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን፤የአፍሪቃ ህብረት ኮሚሽን፤የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት እና የአፍሪቃ የኢኮኖሚ ልማትና ፕላኒንግ ተቋም በጋራ ያዘጋጁት ጉባኤ ነው፡፡

በዚህ ጉባኤ ላይ አንቶንዮ ፔድሮ እንደገለጹት የአፍሪቃ ሀገራት ዘርፈ ብዙ ችግሮች እያጋጠማቸው እንደሆነና እነዚህ ችግሮች እስከ ዛሬ ድረስ የተመዘገቡ የልማት ቱሩፋቶችን ወደ ኋላ እንደቀለበሱት ተናግረዋል፡፡

ነገር ግን አፍሪቃ ተገቢውን ድጋፍ ብታገኝ የዘለቂ ልማት ግቦችን የማሳካት እድሎች እንደሚኖሩ ዋና ጸሀፊው አክለው ተናግረዋል፡፡

በአፍሪቃ በርካታ የተፈጥሮ ሀብቶችና እድሎች እንዳሉ የተናገሩት ዋና ጸሀፊው ሆኖም ግን እነዚህን እድሎችና የአፍቃውያን የፈጠራ ሀብቶች በማቀናጀት ወደ ዘላቂ ልማት ግቦች ለመቀየር የሚያስችል ድጋፍ ማድረግ ለነገ የሚተው አይደለም ብለዋል፡፡

በአህጉሪቱ ያለውን የውሀና የሀይል ለአፍሪቃ ኢንዱስትሪ ልማትና አካታች የኢኮኖሚ ሽግግር መዋል አለበት በሚለው ጉዳይ ላይ ዋና ጸሀፊው እንደተናገሩት የተባበሩት መንግስታት የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት ሆነ የአፍሪቃ የ2063 አጀንዳን ለማሳካት ከተፈለገ የውሀ ሀብት ቁልፍ ጉዳይ ነው ብለዋል፡፡

ለአብነትም ያክል የግሬት ብሉ ዎል ኢኒሽየቲቭ የአፍሪቃ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ከሌሎች አጋሮች ጋር በመሆን በምእራብ ህንድ ውቅያኖስ

ዙርያ የብሉ ኢኮኖሚን ለማፋጠን ጥረት በመደረግ ላይ መሆኑን ዋና ጸሀፊው ተናግረዋል፡፡ ኢነርጂን አስመልክቶ ዋና ጸሀፊው እንደገለጹት እ.አ.አ በ2050 የተቀመጠው የበካይ ጋዝን ዜሮ ለማድረግ የተያዘው እቅድ በ2030 የተቀመጠው አለም የኤልክትሪክ ተደራሽነት ለሁሉም ግብ ካለተሳካ የ2050 ግብ ሊሳካ እንደማይችል አስጠንቅቀዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት የታዳሽ ኀይል ኢንቨስትመንት በአፍሪቃ ከ1.5 በመቶ እንደማይበልጥ የተናገሩት ዋና ጸሀፊው ይህንን አሀዝ ለማሳደግ አፍሪቃውያን ምቹ የሆኑ ፖሊሰዎችንና ደንቦችን ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል በማለት ምክረ ሀሳባቸውን ለግሰዋል፡፡

ለአብነትም ያክል አፍሪቃ የግሪን ሀይድሮጅን ስፔስ ሀብትን በመጠቀም እ.አ.አ በ2035 አፍሪቃ ከዚህ ሀብት 1 ትሪሊዮን ዶላር ማግኘት እንደምትችል ተናግረዋል፡፡ ተቋማቸው የአፍሪቃ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ከተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ሀይ ሌቭል ሸምፒየንና ከሌሎች የቀጠናው ተቃማት ጋር በጋራ በመስራት የአፍሪቃን የግሪን ሀይድሮጅን አልያንስ አባላትን በመደገፍ ላይ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ይህ ተግባራዊ ከሆነ ለአባል ሀገራት የተጨማሪ 122 ቢሊየን ዶላር ወደ ጂዲፒ እንደሚገባላቸው እና እ.አ.አ በ2050 ለአራት ሚሊዮን ዜጎች የስራ እድል እንደሚፈጠር ተናግረዋል፡፡ የታዳሽ ሀይል እምቅ ሀብት ብቻ ሳይሆን በአፍሪቃ ያለው አዋጭነቱም የተረጋገጠ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የአለም የታዳሽ ሀይል ገቢ እ.አ.አ በ2030 ወደ 2 ትሪሊየን ዶላር ይደርሳል ተብሎ የሚገመት ሲሆን የዚህ አስር በመቶ ወይም 200 ቢሊየን ዶላር ወደ አፍሪቃ ኢኮኖሚ ይገባል የሚል እሳቤ አለ፡፡

# የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አዲስ አበባ ከሚገኘው የቤኒን ኤምባሲ ጋር በጋራ ለመስራት በሚያስችሉዋቸው ጉዳዮች ላይ ተወያዩ፡፡




**በስታፍ ሪፖርተር**

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ( አዲስ ቻምበር) አለምአቀፍ የንግድ ትስስርን ለማጠናከር በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም ምክር ቤቱ ከተለያዩ የውጭ ሀገራት ጋር አብሮ ለመስረት የሚያስችለውን ስምምነቶች በመፈራረም በንግድና ኢንቨስትመንት በንግድ ትርኢት ማሳፋፋት፤ በሌሎችም የቢዝነስ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

በቅርቡ ምክር ቤቱ በቤኒን የሚገኘውን የንግድና ኢንቨስትመንት እድሎችንና አማራጮችን ለመጠቀም የሚያስችለውን ውይይት አካሂዷል፡ ፡ ውይይቱ የተካሄደው አዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ጸሀፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያምና በኢትዮጵያ የቤኒን አምባሳደር በሆኑት ሀርቬይ ዲ..ጆክፔ መካከል ነው፡፡

በዚህ የውይይት መድረክ ላይ የንግድ ምክር ቤቱ ዋና ጸሀፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያም ንግድ ምክር ቤታቸው ስለሚያከናውናቸው ተግባራት የገለጹ ሲሆን በተለይም ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ከተለያዩ የአለማችን ሀገራት ጋር በጋራ በመስራት ላይ እንደሆኑ ተናግረዋል፡፡ በተመሳሳይ አምባሳደር ሀርቬይ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የንግድና ኢንቨስትመንት እድሎችን ለመጠቀም የሚያስችል የጋራ ስራ መስራት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡